***Without forgiveness, we will not achieve peace.***

1. ይህ ድርጅት፡ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ነፃ  የሆነ፡ እንደዚሁም ቀለምን ፤ ዘርን፤ ጎሳና ዜግነትን የማይለይ በሁሉም ዓለም ዙርያ የሚገኙ ሴቶች፡ ፍቅር ሰላምና ዕድገት እንዲኖራቸው የሚያበረታታ ማሕበር ነው።

2. ሰላም በዓለም መንገስ እንዲችል፡ ልጆቻችን ከልጅነታቸው ጀምረው የፍቅርና የሰላም ካባ ለብሰው አድገው፡ ለሚቀጥለው ትውልድ የፍቅር መረባቸው ሰፍቶ ሰላም የነገሰባት ዓለም እንዲፍጥሩ መንገድ የሚከፍት መሆኑን በማመን ለዚህ ደግሞ የሁላችን ወላጆች ፈንታ ቢሆንም ሴቶች የላቀ ድርሻ አላቸው ብሎ ያምናል።

3. ይህ ድርጅት በተለያዩ ሃገሮች የሚገኙትን ሴቶች ዕድገት፡ ፍቅርና ሰላም እንዲኖራቸው የሃሳብና የሞራል ድጋፍ ይሰጣል። የማተሪያል ድጋፍ በሚያስፈልግበት ጊዜ ደግሞ እህቶቻችን በፍላጎት እንዲረዳዱ ያስተባብራል።

4. ከዚህ ድርጅት ዋና ዓላማዎች አንዱ አስተማሪ የሆኑ ልምዶቻችን በየራሳችን ፍላጎት እንድንለዋወጥ፡ ሃሳባችንን ሰጥተን መቀበል የሚስችለንን መድረክ ስለሆነ፡ አስተማሪ ነው የምንለውን አሁን ያለን ወይም ያካበትናቸውን ልምዶች፡ በቃል ይሁን በጽሑፍ ለማቅረብ የሁላችን ሃላፊነት እንዲሆን ያደርጋል።

5. በየዓመቱ ጥር 22 ቀን፡ ፍቅራችንና አንድነታችን የምናድስበት ዓመታዊ በዓላችን ይሆናል።